# እስከ መቼ ?

muziky68@yahoo.com

መጋቢት 15 1999

መጋቢት 14 ቀን 1999 በአነ ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል ላይ የቀረበውን ክስ የሚያዳምጠው ፍርድ ቤት ለሶስተኛ ጊዜ ብይን የሚሰጥበትን ቀነ ቀጠሮ ለመጋቢት 21 እንደገና አስተላልፎታል። ፍርድ ቤቱ ብይን የሚሰጥበትን ቀነ ቀጠሮ ያስተላለፈው ዋናው ዳኛ አቶ ያዲል ስላልተገኙ እንደሆነ ተዘግቧል።

በአቶ መልስ ዜናዊ የሚመራው የኢሕአዴግ መንግስት ሰላምና እርቅ ይመጣ ዘንድ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጥሪ ቀርቦለታል። ባለፉት አምስት ቀናት እንኳን ዘጠኝ የሚሁኑ አንጋፋ የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት የሕሊና እስረኞች ተፈተው በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሂደት እንዲጀመር ጠይቀዋል። ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲንም ጨምሮ ከሃይ በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ የሲቪክና የሜዲያ ግሩፐች ኢሕአዴግ

- የሕሊና እስረኞችን በአስቸኳይ አለአንዳች ቅደመ ሁኔታ እንዲፈታ
- ከዚያም በቅንነት ለሰላማዊ ድርድር እራሱን እንዲያቀርብና
- ለሕግ የበላይነት ለዲሞክራሲ ስርዓት መገንባትና ለሰብዓዊ መብቶች ፍጹም መከበር እራሱን እንዲያስገዛ

በአክብሮት መማጸናቸውን በተለያዩ ድህረ ገጾች አንብበናል።

አቶ መለስ ዜናዊ የእሥረኞች ጉዳይ በፍርድ ቤት እየታየ እንደሆነና ኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዳለ ሳያፍሩ በድፍረት ሲናገሩ ተደምጠዋል። የካቲት 12 ፤ የካቲት 26 እንዲሁም መጋቢት 14 1999 በፍርድ ቤቱ አዳራሽ የታዩት አስቂኝ ድራማዎች አቶ መለስ ዜናዊ እንዳሉት ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ሕግ ሞቶ እንደተቀበረና ዜጎች ፍትሕ የሚያገኙበት መድረክ እንደሌለ በተጨባጭ አረጋግጠዋል።

ከራስ ካሳር እስከ ሞያሌ ከወልወል እስከ አሶሳ፤ በደጋው በወይና ደጋው በቆላው በገጠርና በከተማ የምንኖር ክብራችንንና  አገራችንን ጥለን በስደት ያለን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ካቀረቀርንበት ቀና ብለን ኢሕአዴግ በአገራችን ላይ እያደረገ ያለውን አሳፋሪ ጨዋታ "እምቢ አሻፈረን" የምንለበት ጊዜ አሁን ነው። እግዚአብሄር ኢትዮጵያውያን አድርጎ ሲፈጥረን እየታሰርን ፤ እየተደበደብን ፤ እየተገደልንና እየፈራን አቀርቅረን እንድንኖር አይደለም።

**" ፍርሃትና ትግል አብረው አይሄዱም "**

ኢንጂነር ሃይሉ ሸዋል

እስከመቼ በተወለድንባትና እትብታችን በተቀበረባት አገር ተዋርደን እንኖራለን ? እስከመቼ ለሰብዓዊነት ክብር የሌላቸው ሕዝብንና እግዚአብሄርን የማይፈሩ ሰዋች በህዝባችን መካከል የጥላቻን ዘር ሲዘሩና ሲያምሱን ዝም ብለን እናያለን ? እስከመቼ በመንደራችን የወገናችን ደም ሲፈስ ከንፈር መጣጩች ብቻ ሆነን እንቀመጣለን? እስከመቼ ከብሶትና ከምሬት የተነሳ የምንወዳትን አገር ጥሎ ለመሄድ የኤምባሲዎችን ደጆች እናጣብባለን ? እስከመቼ በፍርሃት እንኖራለን ?

ክቡር ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሊቀመንበር፡

> ***"እሥር ቤት ማለት በግንብ በተሰሩ ረጃጅም ጊቢ ውስጥ መቀመጥ አይደለም። አንድ ሰው በአገሩ በነጻነት መናገር፤ መጻፍ ካልቻለ፤ የወረዳ የክልል የአገር አስተዳዳሪዎቹን የመሾምና የመሻር መብቱን ከተነፈገ ያ ሰው እሥረኛ ነው"***

ብለው በምርጫ ውድድር ዘመቻ ወቅት ሕዝቡን ባስተማሩበት ጊዜ የ"እሥር ቤትን" አዲስ ትርጉም ሰጥተውናል። እንደ ኢንጂነሩ አዲስ ትርጉም ከሆነ መላው የኢትዮጵያ ግዛት እሥር ቤት ነው።

በበኩሏ ***"ሰው አለ ነጻነት ምንድን ነው ?"*** ትለናለች ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ (የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ም/ሊቀመንበር) ። በሌላ አባባል "እኔ አይደለሁም የታሰርኩት። በመንደራቹህ ክብራችሁን የተገፈፋቹህ ፤ ቀና ብላቹህ ስላያቹሃቸው ለሆዳቸው ባደሩ የደህንነት አባላት የምትደበደቡ ፤ "ለእውነትና ለፍትህ ብንቆም ከሥራ እንባረራለን" ብላቹህ ጸጥታን የመረጣቹህና ሕሊናችሁን በመሸጥ አንገታችሁን የደፋቹህ ሁሉ እሥረኞች ናችሁ" ማለቷ ነው።

የሰላም የኖቤል ተሻላሚና የዲሞክራሲ ጀግና የሆነችው በአሁኑ ጊዜ እንደነ ብርቱካን ሚደቅሳ በእሥር ላይ የምትገኘዋ የበርማ(ሚሪያማር) ተወላጇ ወ/ሮ አንሳ ሱኪ :" ***ዋነኛውና ብቸኛው እሥር ቤት ፍርሃት ነው። እውነተኛው ነጻነትም ከፍርሃት ነጻ መውጣት ነው"*** ትለናለች። ለዚች የሰብአዊ መብት ተከራራሪ ወይዘሮ የሰው ልጅ በፍርሃት የሚኖር ከሆነ የታሰረ ፍጥረት ነው።

በፍርሃት የታሰረ ሰው በህይወቱ ቁም ነገር ሳይሰራ ያልፋል። ሳያውቀውና ሳያስበው ለሚፈራው ነገር ባሪያ ሆኖ እድሜውን ይጨርሳል። ፍርሃት ሰዎች እግዚአብሄር ሲፈጥራቸው በውስጣቸው ያስቀመጠውን ጸጋ እንዳይጠቀሙበት የሚያፍን አደገኛ የእድገት ጸር ነው። ፍርሃት ሰዎች መድረስ ወደ ሚችሉበት ደረጃ እንዳይደርሱ ከማሸመድመድ አልፎ ተቀብረው እንዲኖሩ የሚያደርግ የሰው ልጆች ዋነኛ ጠላት ነው።

የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በአሁኑ ጊዜ ከአሥር ሺሆች የማያልፉ ግለሰቦች ከ 77 ሚሊዮን በላይ የሆነውን ሕዝባችንን እያመሱት ያሉት በአገርና ከአገር ውጭ ያለነው

ኢትዮጵያዊያን ስለ ፈራናቸው ነው። በአገር ውስጥ ያለነው ገና ለመብታችን ስንነሳ ልጆቻችንን በፊታችን ይደፏቸዋል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩትን ወጣቶቻችንን በግፍ ያጉሯቸዋል። (ግፈኛ የሚባለው ደርግ እንኳን ናዚዎች እንዳደረጉት በመቶ ሺህ የሚቆጠሩትን አፍሶ አልወሰደም።)

ይህን የግፍ በትራቸውን በሕዝቡ ላይ ያሳረፉት መቀጣጫ እንዲሆን ብለው እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። “ይህን ሕዝብ አንዴ ካቀመስነው አርፎ ይቀመጣል” የሚል እምነት አላቸው። አንድ ልዩ ዝግጅት ከተደረገ ከተሞቻችንን የወታደር ካምፕ ያስመስሏቸዋል። ታንክና ከባባድ የወታደር መኪናዎችን በየቀበሊያችን እያበረሩ፤ የመድፍ አፈሙዞችን ወደ እኛ በማድረግ እንድንፈራቸው የሚያደርጉት ሽብር ዋነኛ መሳሪያቸው ነው።

አንዳንዶቻችን በጥቅም ተይዘናል። ከዚህ ፓርቲ ጋር ባለን መቀራረብ መጠነኛ የኢኮኖሚ መሻሻል አግኝተን ጥቅማችን እንዳይነካ የገዢውን ፓርቲ እከክ እያከክን የምንገኝ ስልጣን ላይ ካሉት ያልተናነሰ ትግሉን እየጎዳን ያለን ብዙዎች አለን። የተመቸን ሊመስለን ይችላል። ዳሩ ግን የመንፈስ በሽተኞችና ባሪያዎች እየሆንን እንደመጣን መዘንጋት የለብንም። ወደ ታች ዝቅ ብለን የደከመውን ለማንሳት እጃችንን መዘርጋት ከተሳነን ፤ “እኔ ካለፈልኝ ሰርዶ አይብቀል” በሚል ሰይጣናዊ መርህ ከተመራን “ሰዎች ነን” ብለን እራሳችንን መጥራት የለብንም። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ፡***”የሰው ልጆች የምንሆነው ከኛ በታች ያሉትን ስንመለከት ነው”*** ይሉናል። ራስ ወዳዶች፤ ለታሰሩትና ለተጠቁት፤ ለተራቡትና ለተጎዱት፤ ሥራ ላጡትና ኑሮ ለከበደባቸው የማናስብና የማንቆረቆር ከሆነ እኛ እንደሞትን አድርገን እንድንቆጥር ነው ፕሮፌሰሩ የሚያስተምሩን።

አንዳንዶቻችን ደግም “ከሥራ ብባረርስ ? ገዢው ፓርቲ በበቀል ቢመጣብኝስ? “ ብለን የምንፈራ አለን። በኢትዮጵያ ነጻነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር ለሚደረገው ትግል በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን አንድ ሕይወታቸውን ሰውተው አልፈው የለም እንዴ ? ታዲያ ለልጆቻችን የተከበረችና የታፈረች አገር ለማስተላለፍ የኛን ድርሻ ለማበርከት ወደኋላ የምንለው ለምንድን ነው? ከሥራ ብንባረርስ ? አገራችን ለሁላችንም የጋር አይደለችም እንዴ ? እነ ሽብሬ ደሳለኝ በጥይት ፊታችን ሲወድቁ እኛ ሰላማዊ የሥራ ማቆም አድማ ሲጠራ እንኳን አለመተባበራችን ምን አይነት ሕዝብ ያሰኘናል ? ለምንስ ነው ተማሪና ታክሲ ነጂ ብቻ የሚደበደበው ? ላብ አደሩ፤ አርሶ አደሩ፤ ነጋዴው ፤ አስተማሪውና የቢሮ ሰራተኛው ትግሉን በድፍረት የሚቀላቀለውስ መቼ ነው? ዋ... ወገኔ ....ዛሬ ወንድምህ ሲሞት ዝም ምትለው ነገ ባንተ የማይደርስ ይመስልሃል?

ብዙዎቻችን በአይምሮዋችን ላይ ኢሕአዴግ በሁሉም ቦታ እንዳለ ፤ እንደሚያስፈራና ግዙፍ እንደሆነ አድርገን እናየዋለን። እራሳችንን ደግም አሳንሰን አቅመ ቢሶች አድርገን እንቆጥራለን። **ፍርሃት ካልተበተበን በስተቀር እንዴት ተደርጉ ነው ጥቂት አፋኞች ለ 17**

**አመታት ከ 4 ሚሊዮን በላይ የሆነዉን የትግራይን ሕዝብ ለ15 አመታት ደግም ከ 70 ሚሊዮን በላይ የሆንነዉን ኢትዮጵያዉን በሙሉ አንቀዉና ረግጠዉ ሊገዙ የሚችሉት ?**

# የገዢዉ ፓርቲ ጉልበት የአጋዚ ጦር ወይንም አሜሪካ ያስታጠቀዉ መሳሪያዉ አይደለም። እኔንና እናንተን ማስፈራራት መቻሉ ብቻ ነዉ።

ሳምሶን ጸጉሩን በተላጨ ጊዜ ሃይሉ ከእርሱ እንደተወሰደ እኛም የኢሕዴግን ጸጉር መላጨት ይኖርብናል። እኛ ፍርሃትን ካወለቅን ኢሕአዴግ ጸጉሩን ተላጨ ማለት ነዉ። እንጂነር ሃይሉ ሸዋል እንዳሉት "ትግልና ***ፍርሃት አብረዉ አይሄዱም***"። ለመብታችን በአፍ ሳይሆን በሥራ የምንነሳበት ጊዜ ነዉ። ፓርላማ አትግቡ ብለን ያሳሰርናቸዉን መሪዎችም የማስፈታት የሞራል ግዴታ አለብን።

ኢሕአዴግ የሞተና የበሰበሰ ድርጅት እንደሆነ እራሱ ኢሕአዴግ ያዉቀዋል። ለዚህም ነዉ እንደ ታረደ በሬ የሚንፈራገጠዉ። ኢሕአዴግ ሕይወት ቢኖረዉ ኖሮ የሰላም ጥሪ ሲቀርብለት ተገቢዉን ሰላማዊ ምላሻ ይመልስ ነበር። ኢሕአዴግ ግን ሞቷል። ወገኖቼ ቀና ብንል ገፍተን የምንጥለዉ ሬሳ ነዉ እየገዛን ያለዉ።

ከዳር እስከዳር ኢትዮጵያዉያን ብንነቃነቅ፤ የዜግነት ግዴታችንን ለመፈጸም ብንነሳ፤ አገራችን እየሄደችበት ያለዉን አቅጣጫ ወደ ቀናዉ መንገድ ማዞር እንችላለን። ከዚህ በፊት ሌሎች ፎክረዉት ተግባራዊ ባያደርጉትም ፡ "ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል መፈክር ፍጹም ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ አገራችንን ማደን እንችላለን።

*ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም !*

**" ፍርሃትና ትግል አብረዉ አይሄዱም "**

ኢንጂነር ሃይሉ ሸዋል